# <u>የዘመናችን ሐዋርያ</u>

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠበቃ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ፣**

ቤተ ክርስቲያን «ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ» ተብሎ በነቢያት የተነገረላት ተስፋ በክርስቶስ የተፈጸመላት መምህሯ ክርስቶስ የሆነላት የእግዚአብሔር ጉባኤ ናት (ኢሳ 54፥13፣ ኤር 31፥33-34፣ ዮሐ 6፥45) ቤተ ክርስቲያን «ወመምህር ዘይትቃወም ለነ» ማለትም «ተከራክሮ የሚረታልን መምህራችን» እያለች መምህሯን፣ ጌታዋን ክርስቶስን የምትሰማና ከሱ የምትማር የክርስቶስ ተማሪ ናት። የቤተ ክርስቲያን መምህር ክርስቶስ ነው። ከክርስቶስ ያላገኘችውን እሱ ያላስተማራትን አትቀበልም፣ ያስተማራትንም አትረሳም አትጠራጠርም።

መምህሯ ክርስቶስ ከሞቱና ከትንሣኤው በፊት የጠራቸውን የጠራቸውን ሐዋርያት ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት መርጦ ሹሞላት አርጓል።ሐዋርያትም በዐይናቸው ካዩት፣ በጆሮአቸው ከሰሙት በእጃቸው ከዳሰሱት ከመምህራቸው የተማሩትን «ሕይወት ተገለጠ አይተንማል እን መሰክራለን» (1ዮሐ 1፥3) እያሉ «በዘርኢነ ወበ ዘሰማእነ ስማእታ ንከውን» ማለትም «ያየነውን ና የሰማነውን እንመሰክራለን» እያሉ እውነትን ለአለም በታላቅ መከራ ውስጥ በኃይልና በተአምራት እየተጓዙ ሰብከው ሐዋርያውያን አበውን ተክተው አልፈዋል። ሐዋርያውያን አበውም ስማቸው እንደሚያመለክተው ከክርስቶስ ሐዋርያት የተማሩ፣ በዐይናቸው ክርስቶስን ካዩ የተማሩ ስማቸውም «ሐዋርያውያን» እስኪባል ድረስ ሐዋርያትን መስለውና አክለው ወንጌልን ሰብከው የሐዋርያትን ቃል በመገንዘብ «ከእኔ የተማርከውን ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ» እንዳለ ለደቀመዛሙርቶቻቸው ወንጌልን አደራ ሰጥተው ወደ ጌታቸው ሄደዋል። ከእነሱም በኋላ ሰማዕታት በደማቸው፣ ሊቃውንት በሕይወታቸው እና በዕውቀታቸው፣ መነኮሳት በጸሎታቸው፣ በልዩ ልዩ ሀብታት ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን እያስተማሩ ደቀመዛሙርት እያፈሩ አልፈዋል ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ይህን ታላቅ የሕይወት አደራ ወንጌልን ከነትርጓሜው ሃይማኖትን ከነሥርአቱ ተረክበው የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተምህሮ ጠብቀው እስከዘመናችን ቆይቶናል።

የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የዚህ ሁሉ ሐዋርያዊ ሀብት ባለቤት ናት። ከላይ የጠቀስናቸው ቅዱሳን መምህራን ትምህርቷ ክፉውን ድል እየነሳች የእውቀት የንባብ ምንጭ ሁና በማገልገል ላይ ትገኛለች «ወንጌልን ከተማዋ፣ መስቀልን አላማዋ» አድርጋ ወደ ጽዮን ስትራመድ ያሳለፈችው ታሪክ መከራ የባዛበት ነበር። ነገር ግን የነጉዲትን፣ የነግራኝን፣ የነድርቡሽን ፍላጻ ተቋቋቁማ ስሟን፣

ክብሯን፣ ታሪኳን፣ ትምህርቷን፣እምነቷን ሥርአቷን ጠብቃ ለዚህ ትውልድ የደረሰችው እግዚአብ ሔር ቤተ ክርስቲያኒቱን በየዘመኑ ቆራጥ ሐዋርያ መተርጉም ሊቅ፣ ከአብራኳ ያስነሳላት ስለነበረ ነው። በነአህመድ ግራኝ ጊዜ ሊቃውንቶቿን ያጣችው፣ መጻሕፍቷ የተቃጠሉባት፣ ልጆቿ የታረ ዱባት፣ እሳት በአካሏ ላይ የነደደባት የኢ.ኦ.ተ ቤተ ክርስቲያን ቁስሏ የደረቀው፣ ትምህርቷና ውበቷ የተመለሰው መጽሐፏ ስለ አንድ ፊንታ መቶ ሰላሳ ስድሳ ሆኖ የተጻፈው ብሔራውያን ኢ ትዮጵያውያን በሆኑት የቁርጥ ቀን ልጆቿ ነበር።

ዛሬም በ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፈተናው ባይቀርላትም እግዚአብሔር ሰው አልነሳትም ። የወንጌልን ጉባኤ በማስፋት ሕይወት መድኃኒት የሆነውን የክርስቶስን ስምና ወንጌል እየሰበኩ ምዕራባውያን የአእምሮ ግብር የጠሉባቸውን እና የአስተሳሰብ ቅኝ ተገዦች የሆኑትን መናፍቃን ን በእግዚአብሔር ቃል በመመከት ቤተ ክርስቲያንን ከከሳሾች ምዕራባውያን የተሰነዘሩባትን የሐ ሰት ክሶች በመሻር ክስ በበዛበት በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ጠበቃዎችን አፍርታለች። ከነዚህ ዕውቅ የወንጌል ሐዋርያት ዋናውና በብዙ ሰዎች ዘንድ «የዘመናችን ሐዋርያ» የተሰኙት ስመ ጥሩው አንደበተ ርቱዕ የኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ጠበቃ የሆኑት ታላቁ የወንጌል ሐዋርያ አ ባ ወልደ ትንሣኤ አያልነት ናቸው።

አባ ወልደ ትንሳኤ አያልነህ የንባብ፣ የቃል፣ የቅዳሴ፣ የቅኔ፣ ትምህርታቸውን እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታዊ ሥርአተ ትምህርት ተምረው ቤተ ክርስቲያናቸውን በሚያገለግሉበት ጊዜ እግዚአብሔር «ንዋይ ኅሩይ» እንዳለው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ለወንጌል ለይቶ አዘጋጃቸው። እ ግዚአብሔር ከሚኖሩበት ገዳም ጠርቶ የቤተ ስቲያኒቱን የተቋማት በር ከፍቶ ካሉበት ገዳም ጠር ቶ ወንጌልን ያስታጥቃቸው ጀመር። ከታላቁና ከስመ ው ሊቅ ከብጹእ አቡነ ጎርጎርዮስ በዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛ ውስጥ የነበረውን ትምህርት ካጠናቀቁ በሁዋላ ወደ አሰብ በመሄድ በአሰብ ምድረ  እንደ መጥምቁ እንደ ዮሐንስ ትምህርታቸውን ጀምረዋል። የዮሐንስ ትምህርት በምድረ በዳ ታቅቦ እንዳልቀረ የአባ ወልደ ትንሣኤ ስብከትም ምድረ ውን እያረሰረሰ አዲስ አበባ ደረ ሰ፤ ከዚያም በመላዋ ኢትዮጵያ አሁን ደግሞ በመላው አለም ተዳርሶ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮ ጳ፣ በአፍሪካ፣ በእስያ፣ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ክፍለ አለማት ሁሉ ለሕዝባችን የዕለት እንጀ ራ፣ የሕይወት መመሪያ ሆኖ ይገኛል።

ታላቁ ሐዋርያ ከአሰብ ወደ አዲስ አበባ የመጡት በጥበበ እግዚአብሔር በዝዋይ ገዳም የተማሩትን ወንጌል እያስተማሩ በሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለአራት አመት የሚሰጠውን ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ለመከታተል ነበር። ያ ዘመን በቤ ተ ስቲያን መድረክ ሕዝብ ሰብስቦ ማስተማር የተጀመረበት የመናፍቃን እንቅስቃሴም ቤተ ስቲያ ንን የሚፈታተንበት ወቅት ስለነበር የአባ ወልደ ትንሣኤ በጥበብና በጸጋ በሞገስና በእግዚአብሔ ር ቃል በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ማደግና መታነጽ ለኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስ ቲያን ትልቅ በረከት ነበር።

አባታችን በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እየተማሩ ማታ ማታ በመላው አ ዲስ አበባ በሚገኙት አድባራት እና ገዳማት በተጀመረው ጉባኤ እየተገኙ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ወ ንጌልን መመገብ ጀመሩ። ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚከሱትን የምዕራባውያን ግርፎች የኑፋቄ አስራት በመመከት፣ በንስሐ በመመለስ ሕዝቡም በእምነቱ እንዲጸና የሚያምነውን እንዲያውቅ ያለመ ታከት መሥራት ጀመሩ። በዑራኤል ቤተ ክርስቲያን፣ በልደታ፣ በእስጢፋኖስ፣ በየካ ቅ/ሚካኤ ል፣ በመርካቶ ተክለ ሃይማኖትና በመላው አዲስ አበባ በሚገኙት አድባራትና ገዳማት፤ በክፍለ ሀገራትም በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በወለጋ፣ በጎንደርና በሌሎችም ክፍላተ ሀገራት ሐዋርያዊ ጉዞ በ ማድረግ የኢ.ኦ.ተ ቤተ ክርስቲያንን እንደተተጠላው አውሬ የሚከሷትን የመናፍቃን እንቅስቃሴ . ..... መርጠው መጽሐፍ አልበው በፍጹም ፍቅርና መንፈሳዊ ቅንአት፤ በጋለ መንፈሳዊ ስሜት የጥ ብቅና ሥራቸውን ተያያዙት። ከእስጢፋኖስ ጋር የነበረ ጌታ አብሯቸው ስለነበረ «ወልደ ትንሣኤ ን በአፍና በመጣፍ ማን ይችላቸዋል» እስኪባል ድረስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተከፈተውን የጠ ላት አንደበት በእግዚአብሔር ቃል ዘግተውታል።

እጅግ ተወዳጅ በሆነ አንደበታቸው ርቱዕ የሆነ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖታችንን ሲሰብኩ ል ቡ ያልተነካ እግዚአብሔር ሆይ ስጦታህ ግሩም ድንቅ ነው ያላለ የለም። በዳዊት አድሮ የቤተ እስራኤልን ነቀፋ ነውር ሸንፈት ጎልያድን በመጣል ያራቀ እግዚአብሔር እንደ አሁኑ ብዙ ሰባ ኪያን በነበሩበት በዚያ ጊዜና ዛሬም የቤተክርስቲያን አምላክ መናፍቃን ወደ ቤተክርስቲያን የሚ ወረወረውን ስድብ በአባ ወልደ ትንሳኤ አድሮ አርቆላታል። ሁሉም እንደሚያውቀው የኢትዮጵ ያ ጠላት ምዕራባዊ የሰበካቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥርአተ አምል ኮ በማነወር ታቦቱን ከጣኦት፣ ስዕሉን ከምስል፣ በቤተ ክርሰቲያን የሚደረገውን ሥርዓት በቤተ ጣዖት ከሚደረገው አምልኮ ባዕድ ጋር ፤ የቤተ ክርስቲያኒቱን ካህናት አርአያ ክህነት ያለውን አ

ለባበስ ከፈሪሳውያን ሕይወት ጋር እያነጻጸሩ ሲሳደቡ የቤተ ክርስቲያኒቱን መንጋ ሲሰርቁ ሕዝቡ የያዘውን የተጠቀመበትን ሥርዓተ አምልኮ፣ በረከት ያገኘበትን ክርስቲያናዊ መገኛ ሥርዓት ሲያስነውሩ ፣ ያስተማሩ፣ ያጠመቁ፣ ያቆረቡ፣ ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የሰጡትን ካህናት ሕዝቡ በጠላትነት እንዲመለከታቸው በእናትና በልጅ መካከል ጥል ሲዘሩ በተጠመቀበት የክርስትና ቤት ላይ ድንጋይ የሚጥል ትውልድ ለማፍራት ሲታገሉ የቤተ ክርስቲያን አምላክ አባ ወልደ ትንሣኤን አስነሳ። «በረከተ ኦርቶዶክስ» በሚለው ቁጥር አንድ አልበም ካቶች ላይ እንደምንሰማው «ታቦት» «ስእል» «ቤተመቅደስ» «ስግደት በቤተመቅደስ» በሚል ርእስ አንቀጸ መጽሐፍትን ጠቅሰው ቤተ ክርስቲያናችንን በእውነተኛ መልኳ እንዲያዩዋት አስተምረዋል። «ዕጣን በፊቴ አጸያፊ ነው» «ጸበል የሚባል ነገር የለም» «በመስቀል መባረክ አይረባም አይጠቅምም» እያሉ ለሚከሱትም «በረከተ ኦርቶዶክስ» ቁ. 2 ላይ ባሉት አራት የትምህርት ካሴቶች ..... የቤተ ክርስቲያኒቱን እውነተኛነት ገልጸዋል። ስለ እመቤታችንም እንደነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እንደነ ቅዱስ ኤፍሬም፣ እንደነ አባ ሕርያቆስ አምልተው አስፍተው በማስተማር ትውልዱ ከናቱ እንዳይርቅ የድንግል ጣዕም ፍቅር በልቡናው እንዲያድር «ወላዲተ አምላክ» «ዘለዓለማዊ ድንግልና» «የእመቤታችን አማላጅነት» «ጽዮን» «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» በሚሉ እና በሌሎችም ርዕሶች ላይ ያቀረቡት ትምህርታቸው ከዘንዶው አፍ ወደ ሕጻኑ ኢየሱስ እናት ወደ ድንግል ማርያም የፈሰሰው የስድብ ውሃ እንዳይሰጥም አድርገውታል (ራእ 12፥13) የስድብ መንፈስ ያደረባቸው የበጉና የሠራዊቱ ባላጋራዎች የሆኑት የምዕራባውያን ቀንዶችና ጅራቶች ተፈትነው ያለፉትን፣ ሩጠው የቀደሙትን፣ ተዋግተው ድል የነሱትን በፈጣሪያቸው ዘንድ የድል አክሊል ተቀዳጅተው ከሱ ጋር በመንበሩ የተቀመጡትን ( ) ቅዱሳንን ሲሳደቡ ኦርቶዶክሳዊው ጠበቃ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ዝም አላሉም «ክብረ ቅዱሳን ቁ. 1» ላይ ባሉት ካሴቶች ላይ ለመላው ዓለም የተሰራጨው «ስግደት ለቅዱሳን» «የቅዱሳን መታሰቢያ ለበረከት ነው» «አማላጅነት» «ተክለ ሃይማኖት» በሚሉ ርእሶች ውሻን ከአንበሳ (ቅዱሳንን ከኃጥአን) ለይቶ ለማየት ላልታደለው የኑፋቄ መንጋ መልስ ሰጥተው ቤተ ክርስቲያናቸውን አኩርተዋል። አሁን ደግሞ የከሳሾችን አንደበት ፈጽሞ ለመዝጋት አይነተኛው መንገድ ሕዝቡ ራሱ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሠረታዊ አስተምህሮ ዶግማና ቀኖና (እምነትና ሥርዓት) ለይቶ አውቆ ራሱን እንደ ጠበቃ የሚያስችል ስልት ቀይሶ ትምህርትን በጽሑፍ ቀርጸው ብሉይን፣ ሀዲሱን መጽሐፍተ ሊቃውንቱን አገናዝበው የቤተ ክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት የሥርዓት መጽሐፍትን ዋቢ (...) አድርገው በማዘጋጀት ማንኛውም ሰው እምነቱን ከሥርዓት፣ ሥርዓቱን ከእምነት፣ ወጉን ልማዱን ከእምነት ከሥርዓት ለይቶ እንዲያው

ቅ፣ መርገመ አሪትን ከበረከተ ወንጌል ለይቶ እንዲመለከት ሌትና ቀን በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ አባ ወልደ ትንሣኤ ( ) በመቶዎች የሚቆጠሩ የቪዲዮና የቴፕ ማስተር ካሴ ቶቻቸው በብዙ ሺህ ተባዝተው ከ 1983 ጀምሮ ሳይቋረጡ በመላው አለም የሕዝበ ክርስቲያኑ ሰ ሌዳ ሆነው የራበው የእግዚአብሔርን ቃል እየተመገበባቸው ይገኛል። አባ ወልደ ትንሣኤ በዚህ ዘመን ለተነሱት ሰባኪያነ ወንጌል ግሩም ምሳሌ ሆነው ተገኝተዋል። አባ ለጥብቅና በራሳቸው ከ ቅዱሳት መጻሕፍት የለቀሟቸው ጥቅሶች በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ወይንም ኮንኮርዶ ንስ ( ) በሌለበት ዘመን ሲቀርብ (...) ሌሎችም ሰባክያን በቅርቡ አግኝተው መናፍቃንን መክተው ባቸዋል።

አባታችን አሁን ያሉት በሰሜን አሜሪካ ሲሆን በመላው የአሜርካ እስቴቶች፣ በአፍሪቃ፣ በአው ሮፓ፣ በካናዳና አውስትራሊያ እየተዘዋወሩ በዕርፈ መስቀል እያረሱ ወንጌልን ይዘራሉ። ለሁለት ዓመታት ያክል ከአገልግሎት ብዛት የተነሳ ለራሳቸው በቂ ዕረፍት ስላልነበራቸው በጸና ታመው ነበር፤ ቤተ ክርስቲያንም በጸሎቷ ስታስባቸው ከቆየች በሁዋላ የእግዚአብሔር ምሕረት በዝቶላ ቸው ከሕመማቸው ተፈውሰው በፍጹም ጤንነት ላይ ይገኛሉ። ወደ ጥብቅና ጎራቸው (ወደ ወንጌ ል መድረክ) ከተመለሱም ከዓመት በላይ ሆኖአቸዋል። ስለዚህም እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለ ን። አባታችን የሚኖሩት ገንዘብ በሚመለክበት በአሜሪካ ሲሆን ሕይወታቸው ፍጹም የምናኔ ሕ ይወት ነው። የሚመሩት ሕይወት ከቃላቸው ትምህርት ለመረዳት እንደሚቻለው የኒህ ታላቅ አባ ት ምኞት ገንዘብ ማካበት፤ በሰው ፊት መክበር መሾም መሸለም አይደለም። ብዙ በሚሠራበት በአሜሪካ ትርፋቸው ወንጌል ሆኖ እንደቀደሙት አበው መነኮሳት ከገንዘብ ፍቅር ርቀው፣ ክብረ ስጋን ንቀው፣ ለኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ አንድነት፣ ለእምነቱ እና ለሥርዓቱ መጠበቅ እየሠሩ ይገኛሉ። ይህ ን ሁሉ ሲሠሩ ውዳሴ ከንቱን እየተከናነቡ ሳይሆን ቅዱስ ጳውሎስ «የክርስቶስ ሞቱ በእኛ ሕይ ወቱ በእናንተ ይሠራል» እንዳለ፤ የዕለት ዕለት ኑሮዋቸውን ክርስቶስን በመምሰል በፍጹም ሐዋር ያዊነት ነው። ይህ ትውልድ ጊዜ ይህንን ከመሰሉ አባቶች ሊማር ይገባዋል፤ የሞቱትን እያወሳ ገ ና ያሉትን የሚገድል ሊሆን አይገባውም። ቅዱስ ጳውሎስ ዋኖቻችሁን ተመልከቱ እንዳለን ሁሉ ከአባቶቻችን የሚንማር፤ ወደ ክርስቶስ አገልጋዮች የምንመለከት ያድርጋን።

የቤተ ክርስቲያን አምላክ ያለምስክር አይተወን  አሜን።